# የ J&J የCOVID-19 ክትባት አስተማማኝ ነው

የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት (CDC) እና የU.S. የምግብ እና የመድሃኒት አስተዳደር (FDA) **ከጥልቅ የአስተማማኝነት ግምገማ** በኋላ  የ Johnson & Johnson (J&J) COVID-19 ክትባት አጠቃቀም **ጊዜያዊ እገዳውን አንስተውታል።**

## እኛ የምናውቀው

- **የቨርጂኒያ የጤና መምሪያ** (VDH)  የJ&J ክትባትን **መጠቀም እንደገና ለመጀመር** የCDC and FDA መመሪያን እየተከተለ ነው።
- CDC እና FDA ይህ ክትባት COVID-19ን ለመከላከል **አስተማማኝ እና ውጤታማ** እንደሆነ ሙሉ እምነት አላቸው።
- እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ የክትባቱ **የታወቁ እና  እምቅ ጥቅሞች** ሊያስከትለው ከሚችለው አደጋዎች ይበልጣል።
- አነስተኛ የደም ህዋስ(ትሮምቦሲስ ከትሮምቦሳይቶፒኒያ ጋር)* ደረጃ ያለው የደም መርጋት የማስከተል እድሉ **በጣም ዝቅተኛ** መሆኑን ዳታ ይጠቁማል።
- CDC እና FDA **ንቁ ሆነው ይጠብቃሉ።**
- ክትባቶች ወረርሽኙን **ለመቆጣጠር ጠቃሚ መሳሪያዎች** ናቸው እና ሁሉም 3ቱም የCOVID-19 ክትባቶች አስተማማኝ እና ውጤታማ ናቸው።

**የJ&J ክትባትን መጠቀም እንደገና ለመጀመር ያሉትን አደጋዎች እና ጥቅሞችን ለመገምገም በተጨማሪ የሚታዩ ፍሬ ነገሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤**

- በU.S. እና በዓለም ዙሪያ የCOVID-19 **ወቅታዊ ሁኔታዎች**
- በU.S.የሚዘዋወሩ **ልዩነቶች**
- ከCOVID-19 ጋር የተያያዙ **ሆስፒታል ተኝቶ መታከም እና ሞቶች**
- ክትባቱን ማግኘት ላይ ያለ **ፍትሀዊነት**



***እድሜያቸው ከ50 አመት በታች የሆኑ ሴቶች** የዚህን ያልተለመደ ነገር ግን ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ክስተት ስጋት እየጨመረ መሆኑን እና ይህ ስጋት ያልታየባቸው ሌሎች የCOVID-19 የክትባት **አማራጮች እንዳሉ** ሊያውቁ ይገባል።

**ለነጻ** የCOVID-19 ክትባት በ **Vaccinate.Virginia.gov** ይመዝገቡ ወይም ይደውሉ በ**877-VAX-IN-VA (877-829-4682)**።

VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH